*መልእክት ሁለት*

## የዘመኑ ራእይ ያለውን የዘመኑን አገልጋይ በቅርበት በመከተል ወደ የዘመኑ አገልግሎት ውስጥ ለመግባት አራት ወሳኝ ጉዞዎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:- 1 ነገ. 18፡21-40፤ 19፡2-12፤ 2 ነገ. 2፡1-14

1. **ኤልያስ የዘመኑ ራእይ ያለው የዘመኑ አገልጋይ ነበር (ተዛ. ሚል. 4፡5-6፤ ሉቃ. 1፡13-17፣ 76-80፤ ማቴ. 17፡1-13፤ ራእ. 11፡3-12)፤ በእያንዳንዱ ዘመን ጌታ ሊፈጽም የሚፈልጋቸው ልዩ ነገሮች አሉት፤ የራሱ ምለሳዎች እና የሚሠራቸው የራሱ ሥራዎች አሉት፤ በአንድ ዘመን የሚያደርገው ልዩ ምለሳ እና ሥራ የዚያ ዘመን አገልግሎት ነው፤ የኤልያስ አገልግሎት ጣዖት ማምለክ እግዚአብሔርን የሚበድል ኃጢአት እንደሆነ ለእስራኤል ልጆች የሚናገር ተጻራሪ-ምስክር መሆን ነበር፤ እስራኤል በሙሉ ጣዖታትን ባመለኩ ጊዜ፣ ያመለኳቸው ጣዖታት ሀሰተኛ አማልክት እንደሆኑና ያሕዌ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደነበር ነገራቸው:-**

   ሀ. የኤልያስ ስም ትርጉም "አምላኬ ያሕዌ ነው" ማለት ነው፤ ይህ ስለ ተልእኮው እና ስለ መልእክቱ ይናገራል፤ እርሱ ከምርኮ በፊት ከነቢያቱ መካከል ዋናው እና ወኪሉ ነበር፣ ድል ነሺም ነበር።

   ለ. በኤልያስ ጊዜ እስራኤል በሙሉ በኣልን ሲያመልኩ ነበር፣ ያሕዌ አምላክ ነው ያለው ኤልያስ ብቻ ነበር፤ የእስራኤል ባድማነት እና ጨለማ በጣም በከፋበት በእስራኤል አሳዛኝ ታሪክ እጅግ ጨለማ ከሚባሉት ጊዜያት ውስጥ በአንድ ወቅት እግዚአብሔር ያስነሣው ነቢይ ነበር—1 ነገ. 18፡19።

   ሐ. በኣልን ማምለካቸው በእርግጥም ሰይጣንን ማምለካቸው ነበር፤ 2ኛ ነገሥት 1፡2 የአቃሮን አምላክ ብዔልዜቡል ነበር ይላል፤ በአዲስ ኪዳን ብዔልዜቡል "የዝንቦች ጌታ" ማለት ነው፣ ይህም የኢጋንንት ገዢ የሆነውን ሰይጣንን ያመለክታል፤ ይህ ስም በአይሁዶች ዘንድ በንቀት ወደ ብዔል ዜቡል ተለወጠ፣ ትርጉሙም "የአዛባ ክምር ጌታ" ማለት ነው—ማቴ. 10፡25፤ 12፡24፤ 27፤ ማር. 3፡22፤ ሉቃ. 11፡15:-

      1. ሰይጣን፣ እንደ የአዛባ ክምር ጌታ፣  ዝንቦች አዛባ እንዲመገቡ በመምራት ባለሞያ ነው፤ የዝንቦች ጌታ ስለሆነም፣ ኃጢአተኞች ሁሉ "አዛባ ለመመገብ" ሰይጣንን እንደሚከተሉ ዝንቦች ናቸው፤ የአዳም የወደቁ ዘሮች ሁሉ ኃጢአቶችን እንዲያደርጉ የሚመራቸው እና "የኃጢአት ባሪያ" የሚያደርጋቸው የሰይጣን ምርኮኞች ናቸው—ዮሐ. 8፡34።
      2. ቀድሞ በሆነ ወቅት ለእርሱ ትርፍ የነበሩትን ነገሮች ክርስቶስን ለማትረፍ እንደ "ጉዳት" (ዝቃጭ፣ ቆሻሻ፣ ጉድፍ፣ የውሻ ምግብ፣ አዛባ) እንደቆጠራቸው የተናገረውን የሐዋርያው ጳውሎስን ምሳሌ መከተል ያስፈልገናል—ፊልጵ. 3፡5-8።

   መ. አክዓብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ነገሥታት ይልቅ ያሕዌን አስቆጣ፤ ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆች ከጣዖት አምልኮ የተነሣ እንደተቸገሩ እና ያሕዌ ብቻ አምላክ እንደሆነ እንዲያውቁ ኤልያስን አስነሣው—1 ነገ. 16፡33፤ 18፡4፣ 17-18፣ 37:-

      1. እንደ አዲስ ኪዳን አማኞች፣ ለሐዋርያው ዮሐንስ ቃል መጠንቀቅ ያስፈልገናል—"ልጆች ሆይ፥ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ" (1 ዮሐ. 5፡21)፤ ጣዖታት ክርስቶስን የሚተካ ወይም እውነተኛ፣ ትክክለኛ እና እውን ለሆነው አምላክ ምትክ የሆነን ማንኛውም ነገር ያመለክታል (ዮሐ. 20፡28-29)፤ ሰዉ ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ ማየት ያስፈልገናል (1፡1-2፤ 5፡18፤ 10፡33፤ ሮሜ 9፡5፤ ፊልጵ. 2፡6፤ 1 ዮሐ. 5፡20)።
      2. ያሕዌ ለሕዝቅኤል "የሰው ልጅ ሆይ፥ እነዚህ ሰዎች ጣዖቶቻቸውን በልባቸው አኑረዋል" አለው፤ በልባችን ያለ ጣዖት ከጌታ በላይ የምንወደው እና በሕይወታችን ጌታን የሚተካ በውስጣችን ያለ ማንኛውም ነገር ነው—ሕዝ. 14፡3።
      3. *የክርስቶስ ተቃዋሚ* የሚለው ቃል፣ *ተቃዋሚ* የሚለው የግሪኩ ቅጥያ ሁለት ዋና ትርጉሞች አሉት—አንደኛ፣ "ተጻራሪ" ማለት ነው፤ ሁለተኛ፣ "በዚያ ቦታ" ወይም "በምትኩ" ማለት ነው፤ የክርስቶስ ተቃዋሚ መሆን በአንድ በኩል የክርስቶስ ተጻራሪ መሆን ሲሆን፣ በሌላ በኩል በክርስቶስ ምትክ የሆነ፣ ክርስቶስን የሚተካ ነገር ያለው መሆን ነው—1 ዮሐ. 2፡18-19።
      4. በክርስቶስ ተቃዋሚው መርህ፣ የተቀባውን እና የሚቀባውን ክርስቶስን በመተካት መርህ የሆነ ኑሮ ያለን ከመሆን እንዲያድነን ጌታን መጠየቅ ያስፈልገናል፤ በክርስቶስ ተቃዋሚው መርህ የሆነ ኑሮ ያለው መሆን "የቅባቱ-ተጻራሪ" የመሆን መርህ ኑሮ ያለው መሆን ነው፣ ይህም በውስጣችን ያለው የሦስታንዱ አምላክ እንቅስቃሴ፣ ሥራ እና መሙላት "ተጻራሪ" መሆን ነው—ቁ. 20፣ 27።

5. የሰይጣን ኢላማ ከብዙ ጣዖታት እና ኃይማኖቶች ጀርባ በመደበቅ ከሰዎች አምልኮ መቀበል ነው (ማቴ. 4፡8-9)፤ ጣዖታት ከጀርባቸው የሚደበቁ ክፉ መናፍስት እና አጋንንት አላቸው ምክንያቱም ሰይጣን ከጀርባቸው ነውና፤ ሰይጣን አምልኮን ከእግዚአብሔር ሊሰርቅ እየሞከረ ስለሆነ አብ የሚያመልኩትን እየፈለገ ነው (ዮሐ. 4፡23-24፤ ተዛ. 1 ዮሐ. 2፡20፣ 27)።

ሠ. ኤልያስ የእግዚአብሔርን ምስክር ለመጠበቅ ለራስ ሕይወት ግድ ያለመሰኘትን መርህ ይወክላል፤ በንጉሡ፣ በሕዝቡ እና በአራት መቶ ኃምሳዎቹ የበኣል ነቢያት ፊት ለመቆም ጠንካራ እና ደፋር ነበር፤ ቤተ ክርስቲያን ባድማ ስትሆን እና ብዙኃኑ አማኞች ለብ ያሉ ሲሆኑ፣ እግዚአብሔር ለራሳቸው ሕይወት ግድ የማይሰኙ እና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ግድ የሚሰኙ ተጻራሪ-ምስክር የሚሆኑ ድል ነሺዎችን ያስነሣል (እንደ "አንቲጳስ፣ ሰይጣን በሚኖርበት በእናንተ ዘንድ የተገደለው ምስክሬ፣ የታመነው" አይነት [ድልነሺዎች])—ራእ. 2፡13-14፤ 12፡11።

## II. ያዕቆብ 5፡17 እና 18 "ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች" ይላል፡-

ሀ. ኤልያስ "አጥብቆ" መጸለዩ ቃል በቃል ሲተረጎም "በጸሎት ውስጥ ጸለየ" ማለት ነው፤ ይህ የሚያመለክተው ኤልያስ የጸለየበት ከጌታ የሆነ ጸሎት ለኤልያስ ተሰጥቶ ነበር ማለት ነው።

ለ. ከውጫዊ ሁኔታዎች በመነሣት በስሜቱ፣ በሃሳቡ፣ በውጥኑ ወይም  በጊዜያዊ ስሜቱ  በግል በመነሳሳት የራሱን አላማ ለመፈጸም አልጸለየም፤ ለጌታ ፈቃድ መፈጸም በጌታ በተሰጠው ጸሎት ውስጥ ጸለየ—ተዛ. መዝ. 27፡4፤ ዮሐ. 15፡7።

ሐ. በቀርሜሎስ ተራራ ኤልያስ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እና ለአራት መቶ ኃምሳዎቹ የበኣል ነቢያት "እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፤ በኣል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ" አለ—1 ነገ. 18፡21፡-

1. ኤልያስ ወደ "የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ" ጸለየ "የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፥ የሚቃጠለውን መሥዋዕቱንም እንጨቱንም ድንጋዮቹንም አፈሩንም በላች፥ በጕድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች"—ቁ. 36-38።
2. "ሕዝቡም ሁሉ ያንን ባዩ ጊዜ በግምባራቸው ተደፍተው፡- እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው አሉ"፤ ከዚያ በኋላም አራት መቶ ኃምሳዎቹ የበኣል ነቢያት በሙሉ ተገደሉ—ቁ. 39-40።
3. ኤልዛቤል ስለዚህ ስትሰማ፣ ኤልያስን ልትገድለው ዛተች፤ ኤልያስ በድካሙ ስለፈራ፣ ነፍሱን ሊያድን ሸሸ፤ እስከ እግዚአብሔር ተራራ፣ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ተጓዘ፣ እዚያም ወዳለ ዋሻ ሄደ፣ በዚያም አደረ—19፡2፣ 9-10።

መ. ኤልያስ በእግዚአብሔር ተራራ ሳለ፣ ድንገት ያሕዌ አለፈ፣ ያሕዌ ግን በነፋሱ፣ በምድር መናወጡ ወይም በእሳቱ ውስጥ አልነበረም፤ ከእሳቱም በኋላ እግዚአብሔር በ "ትንሽ የዝምታ ድምፅ" ውስጥ ለኤልያስ ተናገረ፤ ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በማንጎዳጎድ ሳይሆን በእርጋታ እና በዝምታ ለሕዝቡ ወደሚናገርበት ወደ አዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ኤልያስን እያስገባው እንደነበረ ነው—ቁ. 11-12፤ ሮሜ 8፡6፤ 2 ቆሮ. 2፡13፤ 1 ዮሐ. 2፡27።

ሠ. እግዚአብሔርም "እኔም ከእስራኤል ጕልበታቸውን ለበኣል ያላንበረከኩትን ሁሉ፥ በአፋቸውም ያልሳሙትን ሁሉ፥ ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ" አለ (1 ነገ. 19፡18፤ ሮሜ 11፡2-5)፤ እነዚህ የታመኑ ምስክሮች የእርሱ "ስውሮች" ናቸው (መዝ. 83፡3)፣ አምላካችንም "ራሱን የሚሰውር አምላክ" ነው (ኢሳ. 45፡15)።

## III. ኤልሳዕ ኤልያስን ከጌልጌላ እስከ ቤቴል፣ ከቤቴል እስከ ኢያሪኮ፣ ከኢያሪኮ እስከ ዮርዳኖስ ወንዝ መከተሉ ወደ አዲስ ኪዳን ዘመን አገልግሎት ለመግባት፣ በዘመኑ አገልግሎት መሠረት የዘመኑን አገልጋይ ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መልኩ መከተል እንዳለብን ያሳያል፤ ይህን ለማድረግ  በአራት ወሳኝ ቦታዎች በኩል ጌታን መከተል አለብን—1 ነገ. 2፡1-14፡-

ሀ. ኤልያስ ከብሉይ ኪዳን ኢኮኖሚ ጋር የብሉይ ኪዳን ዘመን ምሳሌ ነው፣ ኤልሳዕ ከአዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ጋር የአዲስ ኪዳን ዘመን ምሳሌ ነው።

ለ. ዘመኑ የተለወጠው የእግዚአብሔር ሕዝብ ሥጋቸውን ለማስወገድ በተገረዙበት ስፍራ በጌልጌላ በማለፍ ነበር፤ ስፍራው ሥጋ የተፈረደበት እና ሥጋን እንድናስወግድ እግዚአብሔር ለእኛ ብርሃን የሚሰጥበት ስፍራ ነው—ኢያ. 5፡2-9፤ ገላ. 5፡24፤ ፊልጵ. 3፡3-8፡-

1. ሥጋ ከውልደታችን ጀምሮ ያለን ነገር ሁሉ ነው (ዮሐ. 3፡6)፤ ሥጋ የወደቀው ሦስት ክፍል ያለው ሰው ፍጹም መገለጥ ነው፣ በመንፈሳችን ያለው መንፈስ የሦስታንዱ አምላክ ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ እውን መሆን ነው፤ የወደቀው ሥጋ ጠንካራው እና ክፉው የእግዚአብሔር ጠላት ነው (ሮሜ 7፡5—8፡13)፣ በእግዚአብሔርም ሙሉ በሙሉ እና ፍጹም የተጠላ ነው (ዘፍ. 6፡3፤ 1 ቆሮ. 2፡14-16፤ 3፡1፣ 3)።

2. ከውልደታችን ጀምሮ ያለን ነገር ሁሉ—ኃጢአት፣ ርኩሰት እና መበላሸት ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ መልካምነት፣ ቸርነት፣ ተሰጥኦ፣ ቅንዓት፣ ጥበብ እና ችሎታ—እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ነው።
3. *ሥጋን መቃወም የመንፈሳዊ ሕይወት ከፍተኛው መገለጥ ነው፤ ሥጋን መቃወም ያልተማሩ ሁሉ በመንፈሳዊ መንገድ ላይ [መራመድ] አልጀመሩም፣ መንፈሳዊ ሕይወትንም የእውነት አያውቁም።*

ሐ. ዘመኑ የተለወጠው እግዚአብሔርን እንደ ሁሉ ነገር በመውሰድ ዓለምን የምንተውበት እና ሙሉ በሙሉ ወደ እግዚአብሔር የምንዞርበት ስፍራ በሆነው በቤቴል በኩል በማለፍ ነበር፤ ቤቴል በዓለም ላይ ድል መቀዳጀትን ያመለክታል—ዘፍ. 12፥8፤ 1 ዮሐ. 2፥15፦

1. በዘፍጥረት 12፥8 መሠረት፣ ቤቴል አብርሃም መሠዊያ የሠራበት ስፍራ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረጊያ እና መገናኛ ስፍራ ነው፤ ራሳችንን ለእግዚአብሔር የምንሰጥበት እና ዓለምን ድል ለመንሣት ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የምንሰጥበት ስፍራ ነው—13፥3-4።
2. በዓለም ላይ ድል መቀዳጀት ለመነጠቅ እና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመቀበል ቅድመ ሁኔታ ነው፤ አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት እና ለመነጠቅ ከፈለገ፣ ዓለምን ለመተው ዋጋ መክፈል እና ሙሉ በሙሉ በመስጠት በመሠዊያው ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ መማር አለበት።

መ. ዘመኑ የተለወጠው በኢያሪኮ በኩል በማለፍ ነበር፤ ኢያሪኮ ኢያሱ እና የእስራኤል ሕዝብ ወደ መልካሚቱ ምድር ሲገቡ ማጥፋት የነበረባቸው የመጀመሪያው ከተማ ነበር፣ ይህም የእግዚአብሔርን ጠላት፣ ሰይጣንን ያመለክታል—ኢያ. 6፤ ራእ. 12፥11፦

1. ኢያሱ 6 ትርጓሜው "የተረገመ" ማለት የሆነውን ኢያሪኮን ድል ስለመንሣት ይናገራል፤ ከነዓናውያን በኤፌሶን 6፥12 የተጠቀሱትን በሰማያዊ ስፍራ ያሉትን የክፋት መንፈሳውያን ኃይላትን ያመለክታሉ።
2. ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዢ ነው (ዮሐ. 14፥30)፣ ክፉ መናፍስት የአሁኑን ዓለም የሚያመለክቱት የዚህ ጨለማ ዓለም ገዢዎች ናቸው፤ ክፉ መናፍስት ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ሲያምጽ የተከተሉት እና በዓለም አገራት ላይ አሁን በሰማያዊ ስፍራ እየገዙ ያሉት ያመፁት መላእክት ናቸው—እንደ የፋርስ አለቃ እና የግሪክ አለቃ ያሉት (ዳን. 10፥20)።
3. "የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ" የምንለብስ መሆን ያስፈልገናል (ኤፌ. 6፥11፣ 13)፤ የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር ሁሉ ለማንኛውም የአካሉ ግለሰብ ብልት ሳይሆን ለመላው የክርስቶስ አካል ነው፤ መንፈሳዊውን ውጊያ መዋጋት ያለብን በአካሉ ውስጥ እንጂ እንደ ግለሰቦች አይደለም።
4. ዓለምን ድል የምንነሣበት መንገድ በእግዚአብሔር ቃል ለማመን፣ በቃሉ መሠረት ለማድረግ እና ቃሉን የምናከናውንበትን ውጤቶች እንደምንቀበል ለማመን የእምነት መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ ነው (2 ቆሮ. 4፥13፤ ዮሐ. 17፥17፤ 6፥63፤ ኤፌ. 6፥17-18)፤ ኢያሪኮ በእስራኤላውያን የወደቀው በእግዚአብሔር ቃል በመታመናቸው እና በስፍራቸው ጸንተው በመቆማቸው ነበር፤ ጌታ በዲያቢሎስ ሦስት ጊዜ ሲፈተን፣ ጌታ ሦስት ጊዜ "ተብሎ ተጽፎአል" በማለት መለሰ (ማቴ. 4፥4፣ 7፣ 10)።
5. የክፉ መናፍስትን ጥቃት ድል ለመንሣት፣ ሁሉንም ሁኔታ እና ስሜት ቸል ማለት እና በእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል ለማመን የእምነት መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ አለብን፤ ክርስቶስ በሰጠን ስፍራ፣ በሰማያት መቆም እና ሰይጣንን እና ክፉ መናፍስቱን ወደ ዝቅተኛ ስፍራቸው ማውረድ ጭምር አለብን—2 ቆሮ. 4፥13፤ ኤፌ. 2፥6፤ ቆላ. 3፥1-2።
6. ካህናቱ ታቦቱን በኢያሪኮ መሸከማቸው የሚያመለክተው በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ማድረግ ያለብን የመጀመሪያው ነገር ክርስቶስን ከፍ ከፍ ማድረግ፣ በሁሉም ነገር የመጀመሪያውን ስፍራ፣ ፊተኛውን ስፍራ መስጠት ነው፤ የመለከቶቹ መነፋት እና ጩኸቱ (በከተማው ዙሪያ ለሰባተኛ ጊዜ) የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ቃል ትእዛዝ በእምነት ከክርስቶስ (ከታቦቱ) ጋር የእግዚአብሔርን መመስከር እና መታወጅ ነው—ኢያ. 6፥1-20።

ሠ. ዘመኑ የተለወጠው በዮርዳኖስ ወንዝ በማለፍ ነበር፤ ይህ የአዲስ ኪዳን ጥምቀት የተጀመረበት ወንዝ ሞትን ያመለክታል፤ የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገር በትንሣኤ ለመኖር እና ለማገልገል ሞትን ድል መንሣት ነው—ማቴ. 3፥5-6፤ ሮሜ 6፥3-4፤ ገላ. 2፥20፦

1. የጌታ ጥምቀት ሞትን ያመለክታል፣ ከውኃ ውስጥ መውጣቱ ትንሣኤን ያመለክታል፤ በትንሣኤ ኃይል፣ ጌታ ሞትን ድል ነሣ፤ በመጠመቅ፣ ከሦስት ዓመት ከግማሽ በኋላ ከሚሆነው ከእውነተኛው ሞቱ እና ትንሣኤው በፊት እንኳን በትንሣኤ መኖር እና ማገልገል ችሎ ነበር—ማቴ. 3፥13-17።

2. ዳግም በተወለድን ጊዜ ክርስቶስን እንደዚህ የትንሣኤ ሕይወት አገኘነው፤ ሰው-አምላክ፣ ኢየሱስ፣ በመስቀል ላይ ተቸነከረ፣ በዓመፀኛ ሰዎች እጅም ተገደለ፣ እግዚአብሔር ግን "የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፥ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና"—ሐዋ. 2፡23-24፤ ዮሐ. 11፡25፤ 1 ጴጥ. 1፡3።
3. በሕይወት አዲስነት መመላለስ በጥምቀታችን እውነታ መኖር ነው (ሮሜ 6፡4)፤ በመንፈስ አዲስነት ማገልገል በመጠመቃችን እውነታ ማገልገል ነው (7፡6)።
4. የክርስቶስን የትንሣኤ ኃይል ማወቅን መከታተል ያስፈልገናል፤ ራሳችንን በመካድ መስቀሉን ለመውሰድ የምንቆርጠው እና ከእርሱ መስቀል ጋር አንድ በመሆን ሞቱን ለመምሰል የምንችለው በተፈጥሮአዊ ሕይወታችን ሳይሆን በክርስቶስ የትንሣኤ ኃይል ነው—ፊልጵ. 3፡10-12፤ ማቴ. 16፡24፤ መኃ. 2፡8-10፣ 14።
5. ለመነጠቅ ስንዘጋጅ ሳለን፣ ዮርዳኖስን እንዴት እንደምንሻገርና ሞትን እንዴት ድል እንደምንነሣ መማር አለብን፤ በውስጣችን እና በከባቢ ሁኔታችን የሚኖረውን የሞትን ኃይል እንዴት እንደምንቃወም መማር አለብን፣ በሁሉም ነገሮች ከሞት የተነሣውን ጌታችንን እንደ የትንሣኤ ኃይል በማወቅ እና በመግለጥ ከእርሱ ጋር መጋጠማችንን ማሳየት እና መግለጥ አለብን—1 ቆሮ. 6፡17፤ 2 ቆሮ. 1፡8-9፤ 5፡4፤ 3፡17፤ ተዛ. 4፡5፣ 10-12።
6. የመስቀሉ ሕይወት የሚኖረው በትንሣኤው ኃይል ነው፣ የሚበረታታውም በትንሣኤ ብልጥግናዎች ነው (ፊልጵ. 3፡10)፤ የመኃልየ መኃልይ የመደምደሚያ ቃል የክርስቶስ አፍቃሪ ፈላጊ ውዷ መላውን ምድር የሚሞላውን ጣፋጭ እና ውብ መንግሥቱን (የቅመም ተራራ) ለመመሥረት በትንሣኤው ኃይል (ሚዳቋ እና የዋላ እምቦሳ) ተመልሶ ለመምጣት እንዲፈጥን በመጸለይዋ ነው (መኃ. 8፡13-14፤ ራእ. 11፡15፤ ዳን. 2፡35)።

ረ. የኤልያስን መነጠቅ እና ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጋር የመንፈስን ሁለት እጥፍ ድርሻ ለመቀበል ከፈለግን (2 ነገ. 2፡9-15)፣ በጌልጌላ፣ በቤቴል፣ በኢያሪኮ እና በዮርዳኖስ ወንዝ ማለፍ አለብን፤ በልምምዳችን ዘመኑ ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን እንዲለወጥ፣ ሥጋችንን ማስወገድ (ገላ. 5፡24፤ ፊልጵ. 3፡3)፣ ዓለምን መተው እና ወደ እግዚአብሔር መዞር (ያዕ. 4፡4፤ 1 ዮሐ. 2፡15-17)፣ ሰይጣንን ማሸነፍ (ኤፌ. 6፡10-20፤ ራእ. 12፡11) እና በሞት በኩል በትንሣኤ ወደሆነ ኑሮ ማለፍ (ሮሜ 6፡3-4፤ ገላ. 2፡20) አለብን።

**IV. ይህ የአሁኑ ዘመን የድል ነሺዎች ዘመን ነው፣ በአሁኑ ዘመን አገልጋዮች በኩል የአሁኑ ዘመን አገልግሎት ለድል ነሺዎቹ (የዘላለምን ራእይ ለሚያዩ፣ የዘላለምን ሕይወት ለሚኖሩ እና የዘላለምን ሥራ ለሚሠሩ—ይህ የእግዚአብሔርን ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ ግብ ማየት እና አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን መኖርና መሥራት ነው) የጌታ ጥሪ ድምጽ መሰማት ነው፤ እነዚህ ድል ነሺዎች ለክርስቶስ አካል እውነታ መገንባት፣ ለክርስቶስ ሙሽራ መዘጋጀት እና ለክርስቶስ መንግሥት መገለጥ ናቸው፤ በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት የእግዚአብሔርን ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ ፍላጎት ለማሟላት፣ ድል ነሺዎቹን፣ ሕያው-ንቁዎቹን ለመሆን ቁርጠኛ ውሣኔ መወሠን አለብን—መሳ. 5፡15-16፣ 31፤ ራእ. 2፡7፣ 11፣ 17፣ 26-29፤ 3፡5-6፣ 12-13፣ 21-22።**

© 2022 Living Stream Ministry